# ● መጽሐፈ ድጓ ዘአስተምህሮ ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ●



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ
(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ነሐሴ ፮፣ ፳፻፲፰ ዓ.ም

## ዘአስተምሕሮ

**፻፳፮. እመቤታችን በደብተራ ጳውሊ ትመሰላለች። በየትኛዋ ደብተራ ነው? በዕብራውያን የጠቀሳት ናት ወይስ ይሰፋቸው ከነበሩት?**

መልስ፦ እመቤታችን በደብተራ (በድንኳን) የተመሰለችው ዕብራውያን ላይ በተጠቀሰችው ደብተራ ነው። "ወክርስቶስሰ ዘመጽአ ከዊኖ ሊቀ ካህናት ለእንተ ትመጽእ ሠናይት በውስተ እንተ ተዐቢ ወትኄይስ ደብተራ እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ ወኢኮነት በውስተ ዝ ዓለም" እንዲል (ዕብ.9፥11)። ለዚህም ማስረጃው ሰው ያልሠራት [እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ] የሚለው አገላለጽ ነው። ጳውሎስ ድንኳንን ሰፋ ከተባለ ግን ሰው የሠራት ስለሆነች ለተጠቀሰው ምሳሌነት አትሆንም።

**፻፳፯. ኢየሱስ ክርስቶስ ያልተሠራና ያልተፈተለ ልብስ ነው ሲል ምን ማለት ነው? ዐይኖቹ ከወይን ይልቅ የሚያምሩ፣ ጥርሶቹ እንደበረዶ ነጭ የሆኑ ናቸው ሲልስ ምንን ለመግለጽ ነው?**

መልስ፦ ይህ በትርጓሜ ቋንቋ "ልብስ" ግሥ ይባላል። በቅኔ ቋንቋ ደግሞ "ልብስ" ሰም ይባላል። ክርስቶስን በልብስ መስሎታል። ያልተሠራና ያልተፈተለ ልብስ የሚባለው ሥረ ወጥ ልብስ ነው። ሥረ ወጥ ልብስ የሚባለው ደግሞ ጫፍና ጫፉ እየተሰፋ የሚሠራ ሳይሆን ድርና ድርን ወይም ዘሐና ዘሐን በማዋሐድ የሚሠራ ልብስ ነው። ይህ ልብስ ከተሰፋው ልብስ ይልቅ ጽኑ ነው። የድሩና የድሩ ተዋሕዶም ከተሰፋው ይልቅ የጸና ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም በዚህ መመሰሉ የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ ጽኑ መሆኑን ያመለክታል።

**፻፳፰. ልብሱን በወይን ያጥባል፣ መጎናጸፊያውንም በፍሬ ደም የሚያጥብ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሲል ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ ይህ በብሉይ ኪዳን ለይሁዳ ወልደ ያዕቆብ የተነገረ ቢሆንም በትንቢት ለክርስቶስም እንደሆነ ተነግሯል። ልብሱን በወይን ያጥባል ማለት ሰውነቱ በዕለተ መስቀል በደም እንደሚታለል ያመለክታል። መጎናጸፊያውን በፍሬ ደም ያጥባል ሲል መጎናጸፊያ የተባሉ ምእመናን ናቸው። ምእመናንን በሥጋው በደሙ ያከብራል ማለት ነው (ዘፍ.49፥10-12 አንድምታ ትርጓሜ)።

**፻፳፱. ጭቃና ኩስ የሆንክ የሰው ልጅ ሆይ ራስህን ለምን ከፍ ከፍ ታደርጋለህ ሲል ምን ለማለት ነው?እግዚአብሔር ሰውን አክብሮ ሠራው ከሚለው ጋር እንዴት ይታረቃል? ሰው ግን ከንቱን ይመስላል ሲልስ ሰው የክብሩ ወራሽ አይደለም ወይ ለምን እንዲህ አለ?**

መልስ፦ እውነት ነው እግዚአብሔር ሰውን በአርአያው አክብሮ ፈጥሮታል (ዘፍ.1፥26-27)። የሰው ልጅ ግን ይህን ክብሩን ጠብቆ መኖር ሲገባው ባለመጠበቁ ከክብሩ ወርዶ እንደ እንስሳ ሆነ ተብሏል። "ወዕጓለ እመሕያውሰ እንዘ ክቡር ውእቱ ኢያእምረ። ወኮነ

ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ ወተመሰሎሙ" እንዲል (መዝ.48፥20)። በመሆኑም በምንረግጠው ጭቃና ኩስ ተመስሏል። ከንቱም ተብሏል። ምንም እንኳ በምጽአት ተነሥተን ለዘለዓለም በደስታ በመንግሥተ ሰማያት ብንኖርም በዚህ ምድር ያለን ሕይወት ግን አጭርና የተናቀ በመሆኑና ሥጋችንም በዚህ ዓለም ሳለ እስከ ምጽአት በስብሶ የሚቀር በመሆኑ ቅዱስ ያሬድ በጭቃ በኩስ መስሎ ተናግሮታል።

**፻፴. ወርቅና ብር የእኔ ነው ለወደድኩት እሰጠዋለሁ ሲል ምን ለማለት ነው? ብርን አትውደዱ ከሚለው ጋር እንዴት ይታረቃል?**

መልስ፦ በዚህ ምድር ያለ አካል ያለው ነገር ማንኛውም በተፈጥሮ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው። ወርቅና ብር የእኔ ነው ያለውም በተፈጥሮ ባለቤቱ እርሱ እግዚአብሔር በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር ለፈቀደውም ይሰጠዋል። ብርን አትውደዱ ማለቱ ብር አያስፈልግም ተብሎ አይተረጎምም። ብርን አትውደዱ ማለት ከእግዚአብሔር በላይ አታምልኩት ማለት ነው። በብር አትመኩበት ማለት ነው እንጂ። ስለዚህ ምንም የሚጣላ ነገር የለውም።

**፻፴፩. እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ማረፊያዬ ይላታል ሲል ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር ይወሰናል ወይ?**

መልስ፦ እግዚአብሔር በአካል በሁሉ ቦታ ያለ ነው። በዓለም ሁሉ የሚኖር ዓለምን የሚተርፋት እንጂ የማትተርፈው አምላክ ነው። ቤተክርስቲያንን ማረፊያዬ ማለቱ ግን የጸጋው ግምጃ ቤት በመሆኗ ነው። ረድኤቱን፣ ጸጋውን የሚሰጥበት የተለየች ቦታ በመሆኗ ነው። እግዚአብሔር ጸጋውን በማንኛውም ቦታ በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ መስጠት ቢችልም የበለጠ እርሱ ራሱ ፈቅዶ የሚሰጥባት በመሆኗ ቤተክርስቲያንን ማረፊያዬ ብሏታል (1ኛ ነገ.9፥3)።

**፻፴፪. በሰንበት ቀን ቤተክርስቲያንን ምስጋና ይከባታል ሲል ምን ማለት ነው? ሌሎች ቀን ምስጋና የላቸውም ማለት ነው?**

መልስ፦ ይህ ዓይነቱ አገላለጽ በጸናው መናገር ይባላል። ከሰባቱ ዕለታት በተለየ ሰው ሁሉ ወደእርሷ ተሰብስቦ እግዚአብሔር የሚያመሰግንባት ዕለት ሰንበት ናት። ምንም እንኳ በሌላው ቀንም ምስጋና ቢኖርም በሰንበት ያለው ምስጋና ግን ብዙ በመሆኑ ይህንን ለመግለጽ በሰንበት ቤተክርስቲያንን ምስጋና ይከባታል ተብሏል።

**፻፴፫. ሰንበትን መላእክት በሰማያት ጻድቃን በገነት ያከብሯታል። ባሕር፣ ዓሣዎች፣ አናምርትና ፍጥረታት ሁሉ ያከብሯታል ሲል ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ ባሕርና ሌሎችም ግዑዛን ፍጥረታት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ማለት በእነርሱ ምክንያት እግዚአብሔር ይመሰገናል ማለት ነው እንጂ አፍ አውጥተው

ያመሰግኑታል ማለት አይደለም (መዝ.18፥1)። ዓሣዎች፣ አናምርት፣ አናብስትና ሌሎችም ደማውያን ፍጥረታት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ማለት ደግሞ እርሱ እግዚአብሔር በሚያውቀው እኛ በማንረዳው መልኩ ያመሰግኑታል ማለት ነው።

፻፴፬. ቤተክርስቲያንን የንስር ዐይን ያላያት ሲል ምን ማለት ነው? በሰማይ ላለው አርአያ ናት ሲባልስ እንዴት ነው?

መልስ፡- ቤተክርስቲያን በሰማይ ላለው አርአያ ናት ማለት በሰማይ 24ቱ ካህናተ ሰማይ፣ አራቱ ኪሩቤል፣ ሌሎችም መላእክት በየመዓርጋቸው እንዳሉና እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑ ሁሉ በቤተክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናትና ምእመናን በየመዓርጋቸው እግዚአብሔርን ያመሰግኑታልና ነው። ኪሩቤል የሊቃነ ጳጳሳት፣ ሱራፌል የጳጳሳት፣ አጋእዝት የኤጲስ ቆጶሳት፣ ኀይላት የቆሞሳት፣ አርባብ የቀሳውስት፣ መናብርት የዲያቆናት፣ ሥልጣናት የንፍ*/ቀ ዲያቆናት፣ ሊቃናት የአናጕንስጢሳውያን፣ መኳንንት የመዘምራን፣ መላእክት የዐፀውተ አናቅጽ ምሳሌ ናቸውና (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 9 አንድምታ ትርጓሜ)። የንስር ዐይን ያላያት ሲል ንስር የተባለ ዲያብሎስ ነው። ዲያብሎስ ያላሳሳታት ቤተክርስቲያን ማለት ነው። አንድም በምስጢር ቤተክርስቲያን የተባለች መንግሥተ ሰማያት ናት። ዲያብሎስ ያላያት መንግሥተ ሰማያት አለች ማለት ነው። "ወፍኖት ዘኢርእያ ጎፍ ወኢነጸራ ዐይነ ንስር። ወኢኬድዋ ደቂቀ ዝኁራን" እንዲል (ኢዮ.28፥7-8)።

፻፴፭. ልጁ የወጣትነት ሥራን ተዋት የሚለው ምኑን ነው?

መልስ፡- ወጣትነት የሚባለው የእሳት ባሕርይ የሚሰለጥንበት ወቅት ነው። በዚህ ጊዜ ብዙው ወጣት በዝሙትና በሌሎችም ኃጣውዕ ይፈተናል። ስለዚህ እኒህን በመሳሰሉ ኃጢአቶች አትውደቅ ለማለት የወጣትነትን ሥራ ተው ተብሏል። በበዛው መናገር እንጂ በወጣትነታቸው የጽድቅ ሥራን የሠሩ ደጋግ አባቶችም ነበሩ፣ አሉ፣ ይኖራሉ።

፻፴፮. ዘገብሮ ለሰብእ በአርአያ ዚአሁ ይላል። አርአያና አምሳል ምን ማለት ነው?

መልስ፡- አምሳልና አርአያ አንድ ወገን ነው። በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ተፈጥረናል ማለት እግዚአብሔር በባሕርዩ የሚገዛውን ፍጥረት የሰው ልጅ ደግሞ በጸጋ ይገዛዋልና ነው (ዘፍ.1፥26 አንድምታ ትርጓሜ)።

፻፴፯. ብሔረ ሕያዋንና ብሔረ ብፁዓን ልዩነቱ ምንድን ነው?

መልስ፡- ብሔረ ሕያዋን የሚባለው ከዚህ ምድር ያረጉ እነ ነቢዩ ኤልያስ፣ እነ ሄኖክና ሌሎችም እስከ ምጽአት ድረስ ይኖሩበት ዘንድ የተሰጠ ቦታ ነው። ብሔረ ብፁዓን ደግሞ እንደእኛ የሚጋቡ፣ የሚዋለዱ፣ የሚሞቱ ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ ነው። ቢሆንም ግን ክፋት የሌለበት ደጋጎች ብቻ የሚኖሩበት ዓለም ነው።

፲፴፰. ሀለዉ ዕደው እለ ኢጥእምዎ ለሞት ይላል። እነ ኤልያስ እነ ሄኖክ ወዘተርፈ ሕያዋን ናቸውና ጥምቀታቸው መቼ ተፈጸመ?

መልስ፦ መቼ እንደተጠመቁ የሚገልጽ ምንም ዓይነት መረጃ ሰምቼ አላውቅም። ስለዚህ የዚህን መልስ አላውቀውም።

፲፴፱. አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል ፊታቸውን በትእምርተ መስቀል አማተቡ ሲል አሁን እኛ በጣታችን እንደምናማትበው ያለ ነው ወይስ ሌላ ትርጉም አለው?

መልስ፦ ይህንን ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አላገኘሁትም። ቅዱስ ያሬድ አማተቡ ብሏል። ዝርዝር ታሪኩን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከተጻፈው ውጭ አላውቀውም። [ምናልባት የመስቀል ምልክት በመላእክት ዓለምም ይታወቅ የነበረ ስለሆነ ገብርኤል በመካከላቸው ሲቆም የእርሱን የመስቀል ምልክት ለእነርሱ አድሎ ተናግሮ ይሆን? እኔ እንጃ ዙሮ ዙሮ አላውቀውም]።

፲፵. ነቢያት ሰበኩት ምስክርም ሆኑት ወላዲ አብንም እጅህን ላክ አሉት ሲል ምን ማለት ነው? እጅህን ላክ ሲል ምንድን ነው?

መልስ፦ ወልድ የአብ ክንድ፣ የአብ ኀይል፣ የአብ እጅ...ወዘተ እየተባለ ይጠራል። እጅ ከሰውነታችን ሳይለይ የወደቀን አንሥቶ እንደሚመልስ ሁሉ ወልድም ከአብ ህልውና ሳይለይ ሰውነትን ገንዘብ አድርጎ የሰው ልጆችን አድኗልና እጅ፣ ክንድ ይባላል። ስለዚህ ከሞት፣ ከባሕርይ ጕስቁልና ያድነን ዘንድ ልጅህን ላክ እያሉ ነቢያት ትንቢት ይናገሩ እንደነበር ቅዱስ ያሬድ ገልጾልናል።

፲፵፩. ከዓለም ደስታ የራቀ ክቡር ኤልያስ በንጽሕናና በቅድስና የሥጋውን ቤት ሠራ ይላል። የሥጋውን ቤት ሠራ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ የሥጋውን ቤት ሠራ ቅኔያዊ አነጋገር ነው። ምስጢሩ ሰውነቱን በንጽሕናና በቅድስና አስጌጠ ማለት ነው።

፲፵፪. ኤልያስ ለእግዚአብሔርም የሰላም መሥዋዕትን አቀረበ ይላል። የሰላም መሥዋዕት የሚለው ምንድን ነው?

መልስ፦ የሰላም መሥዋዕት የሚባለው ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የደኅንነት መሥዋዕት ነው። በብሉይ ኪዳን ሰዎች ኃጢአት ስለሠሩ ኃጢአታቸው ይሠረይ ዘንድ የሚያቀርቡት የኃጢአት መሥዋዕት ነበረ። ይህ የኤልያስ መሥዋዕት ግን ከኃጢአት መሥዋዕት የተለየ የእግዚአብሔርን አምላክነት ለሌሎች ለማሳወቅ የተደረገ መሥዋዕት ስለሆነ የሰላም መሥዋዕት ተብሏል።

**፻፴፫. ኤልያስና ዮሐንስ የፍየል ሌጦዎችን ይታጠቃሉ። ኤልያስና ዮሐንስ ኑሯቸውም በገዳም ነው። በወገባቸው መታጠቂያ አለ ሲል ምን ማለት ነው?**

*መልስ፦ ዮሐንስና ኤልያስ በቁሙ ልብሳቸው የፍየል ቆዳ (ሌጦ) ነበር ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ መታጠቂያን ይታጠቁ ነበር። ኑሯቸው በገዳም ነበር መባሉ ብዙ ጊዜያቸውን ያሳለፉት በዱር ስለነበረ ይህንን ለመግለጽ ነው።*

**፻፴፬. ኤልያስ በጸሎቱ ከሰማይ ዝናምን አዘነመ አና ለጎመ ሲል ምን ለማለት ነው? አዘነመና ለጎመ እንዴት ይታረቃሉ?**

*መልስ፦ ነቢዩ ኤልያስ መጀመሪያ እስራኤላውያን በመበደላቸው ምክንያት ዝናም እንዳይዘንብ ጸልዮ ሰማይን ከልክሎታል። በኋላ ደግሞ የሰውን መቸገር አይቶ እንደገና ዝናብ ይዘንብ ዘንድ ጸልዮ አዝንቧል።*

**፻፴፭. ኤልያስ በእሳት ፈረስ ሠረገላ ወደ ሰማይ ዐረገ ይላል። የእሳት ፈረስ እና ሠረገላ ምንድን ናቸው?**

*መልስ፦ በእሳት ፈረሶች የሚጎተት ሠረገላ ኤልያስን ወደሰማይ አሳርጎታል። ያ ሠረገላና የእሳት ፈረሶቹ ከየት እንደመጡና ምን እንደሆኑ ግን ዝርዝር ጉዳይ አላገኘሁም።*

**፻፴፮. ገብርኤል ማለት ከሚለው መጀመርያ ሰው የሆነ አምላክ ነው የሚባለው ወይስ አምላክ የሆነ ሰው? ማለቴ ቅደም ተከተሉ አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ ነው የሚባለው ወይስ እንዴት ነው?**

*መልስ፦ ብእሲ ወአምላክ ሲል "ወ" ቅጽል ናት። ስለዚህ አምላክ የሆነ ሰው ተብሎ ይተረጎማል። አምላክ ወሰብእ ሲል ደግሞ ሰው የሆነ አምላክ ማለት ነው። እንዲሁም "ወ" ዋዌ ሆና "ም" ተብላ ትተረጎማለች። ስለዚህ ብእሲ ወአምላክ ሲል ሰውም አምላክም ተብሎ ይተረጎማል። ምሥጢሩ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን ያመለክታል። አምላክ ሰው ሲሆን በዚያው ቅጽበት ሰው አምላክ ሆኗል። ስለዚህ መቀዳደም ስለሌለ በሁለቱም ቢገለጽ ይሆናል። በትርጓሜያችን እንደምንገልጸው የተዋሕዶው ጀማሪ ቃል ነው። "ቃል ሽቶ ተዋሕዷል እንጂ ሥጋ አልተዋሐደምና" እንዲል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ትርጓሜ)። ይህም ማለት ከተዋሕዶ በፊት ሥጋ እኔ ባይ አልነበረም ከተዋሕዶ በፊት እኔ ባይ የነበረ ቃል ነው ማለት ነው። ከተዋሕዶ በፊት ሥጋ እኔ ባይ ነበረ ካልን ግን ኅድረት የሚል ክሕደትን ያመጣል። የሆነ ሆኖ በጊዜ ተዋሕዶ ግን አምላክ ሰው፣ ሰው አምላክ ሲሆን መቀዳደም ስለሌለ በሁሉም መገለጽ ይችላል።*

**፻፴፯. ኃጢአትን ይቅር የሚል የአንበሳ ልጅ አንበሳ ወልድ ተወለደ ሲል ምን ለማለት ነው?**

መልስ፡- መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተለዋጭ ዘይቤ መግለጽ የተለመደ ነው። ለምሳሌ ዳን ወልደ ያዕቆብ የአንበሳ ልጅ ተብሎ ነበር (ዘዳ.33፥22)። ቅዱስ ያሬድ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን የአንበሳ ልጅ አንበሳ ብሎታል። በዚህ አገላለጹ አብንም አንበሳ ብሎታል ማለት ነው። አንበሳ የማይፈራ፣ ኀዱዕ (ጸጥ ያለ) ነው። እግዚአብሔርም በባሕርዩ ፍርሀት የሌለበት ጥቡዕ፣ ብንበድል ቸኩሎ የማያጠፋን ኀዱዕ በመሆኑ አንበሳ ተብሏል። ይህ የአንበሳ አብ ልጅ አንበሳ ወልድ ከድንግል ማርያም በሥጋ ተወለደ ማለት ነው።

**፻፵፰. እመቤታችን ቤተ መቅደስ ገብታለች (ኖራለች) ስንል በብሉይ ኪዳን ሴቶች ወደ ቤተ መቅደስ ይገቡ ነበር?**

መልስ፡- ቤተ መቅደስ የሚባለው ሰሎሞን ያሠራው ቤተ እግዚአብሔር ነው። ይህም ሕንፃውንም በዙሪያው ያሉ ቤቶችንም ቤተ መቅደስ ማለት የተለመደ ነው። አሁን ከቅጽረ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከሕንፃ ቤተክርስቲያን በተጨማሪ የመቃብር ቤት፣ የፍትሐት ቤት፣ ደጀ ሰላም፣ ቤተልሔምና የመሳሰሉት እንዳሉ ያን ጊዜም በቤተ መቅደስ ዙሪያ ሌሎች ቤቶች ስለነበሩ ድንግል ማርያም በዚያ ትኖር ነበር ለማለት ነው እንጂ ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ጊዜ ከሚገባበት ቅድስተ ቅዱሳን ወይም ሌዋውያን ካህናት ከሚያመሰግኑበት የመቅደሱ ክፍል ትኖር ነበር ለማለት አይደለም። ዙሪያውን ሌሎችም ይኖሩ እንደነበረ ማስረጃው "ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢይት ነበረች። እርሷም ከድንግልናዋ ጀምራ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት ኖረች። እርሷም ሰማንያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና በጣም አርጅታ ነበር። በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር" የሚለው ነው (ሉቃ.2፥36-37)። በእርግጥ ብትገባም ያንስባታል እንጂ አይበዛባትም ነበር። አማናዊት መቅደስ እርሷ ራሷ ናትና። ሰሎሞን በሠራው ቤተመቅደስ እግዚአብሔር በረድኤት ያድር ነበር። በታላቂቱ ቤተ መቅደስ በድንግል ማርያም ግን ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆኖ ከረድኤት በበለጠ በከዊን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ኖሮባታልና።

**፻፵፱. ገብርኤል ማርያምን እንዲያበሥራት የተደረገ በምን ምክንያት ነው?**

መልስ፡- ይህ በትርጓሜ በትውፊት እንደሚነገረው በመላእክት ዓለም ሳጥናኤል አምላክ ሳይሆን አምላክ ነኝ ብሎ ሁከት በፈጠረ ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል አምላካችንን እስክናገኘው ድረስ በያለንበት እንቁም ብሎ መላእክትን በማረጋጋቱ "ሑር አብሥራ ለወለተ ሐና። ሒድ የሐናን ልጅ ማርያምን የደስታ ዜና ንገራት" ተብሎ እንደተነገረ ተጽፏል (አክሲማሮስ አንድምታ)።

**፻፶. ማርያም ግን ይህን ሁሉ ትጠብቀው ነበር ይላል። የምትጠብቀው ምንን ነው?**

መልስ፦ ቅዱስ ያሬድ ማርያም ግን ይህንን ሁሉ ትጠብቀው ነበር ያለውን "ዝኬ ውእቱ ገብርኤል ዘዜነዋ ጥዩቀ" ብሎ አጉልቶታል። ይኸውም ገብርኤል የነገራትን ነው ብሎታል። ትወልጃለሽ ያላትን ከገብርኤል ሰምታ ለሌላ ልናገረው አላለችም ነገሩን አስተውላ በልቧ በምሥጢር ትጠብቀው ነበር ማለት ነው። አረጋዊ ስምዖን ስለጌታ የተናገረውን ትንቢትም ሰምታ በልቧ ታስተውለውና ትጠብቀው ነበር። ምሥጢር ጠባቂነትን ከእርሷ እንማራለን (ሉቃ.2፥19)።

**፻፶፮. ቅዱስ ገብርኤል አበሠራት ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ ደራሲው "እግዚአብሔር እግዚእ ሶበ ለገብርኤል ተመሰሎ" ይላል። አይቃረንም?**

መልስ፦ አይቃረንም። በሁለቱም ያስተረጉማል። አንደኛው ገብርኤል የላኪውን የእግዚአብሔርን ሐሳብ ስለተናገረ በገብርኤል አድሮ የተናገረ ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ እግዚአብሔር ገብርኤልን መስሎ ተናገራት ማለት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ምንም ከእግዚአብሔር ተልኮ ቢናገርም ተናጋሪው ገብርኤል ስለሆነ ገብርኤል አበሠራት ተብሏል።

**፻፶፯. ድንግል ማርያም ገብርኤልን ቃልህን አሰማኝ ድገምልኝ ድገምልኝ አለችው ይላል። ምን ማለት ነው? ገብርኤል ሲያበስራት እንደዚያ ብላው ነበር?**

መልስ፦ በመጽሐፍ ቅዱስ ይህ አልተገለጸም። በትውፊት ግን እንዲሁ ትወልጃለሽ ሲላት ቃሉን ለመረዳት ደግማ እንደጠየቀችው ይነገራል። ድገምልኝ ድገምልኝ የሚለው ለዚህ ነው። በሌላ መልኩ የመጽሐፍ ቅዱሱን ሐሳብ በሌላ አገላለጽ የቀረበ ሆኖም እናገኘዋለን። ትወልጃለሽ ሲላት እንዴት ይሆናል ብላ መጠየቋ ነገሩን የበለጠ እንዲገልጽላት በመሆኑ ይህንን ድገምልኝ በሚል አገላለጽ ቅዱስ ያሬድ ጽፎታል (ሉቃ.1፥34-38)።

**፻፶፰. ክብሮሙ ለመላእክት ከመ መንኰራኵር ወረደ ይላል። የከመ ንጽጽር እዴት ነው?**

መልስ፦ መንኰራኵር የሚለው የሠረገላ ተሽከርካሪው ክፍል (እንደ ጎማ ያለው) ነው። ተጎታቹ ከቦታ ቦታ የሚሔድ በመንኰራኵር አማካኝነት ነው። የመላእክት ክብራቸው እግዚአብሔር እንደ መንኰራኵር ወረደ ማለት ነው። መንኰራኵር ፈጣን እንደሆነ ቀጠሮው እንደደረሰ እግዚአብሔር ፈጥኖ ሰው ሆነ ማለት ነው።

**፻፶፱. ገብርኤል ማለት አምላክ የሆነ ሰው ማለት ነው ሲል ምን ማለት ነው? ገብርኤል አምላክ ነው ወይ?**

መልስ፦ የመላእክት ስም የእግዚአብሔርን ግብረ ባሕርይ የሚገልጽ ነው። ለምሳሌ ዑራኤል ማለት ብርሃነ እግዚአብሔር/ የእግዚአብሔር ብርሃን ማለት ነው። ገብርኤል የሚለው ስም ደግሞ አምላክ የሆነ ሰው ማለት ነው። አንድም እግዚእ ወገብር ሰው

የሆነ አምላክ ማለት ነው። በአጭሩ ስማቸው የእግዚአብሔርን ግብረ ባሕርይ የሚያመለክት ነው እንጂ ራሳቸው አምላክ ናቸው ማለት አይደለም። ስለዚህ ገብርኤል አምላክ አይደለም።

**፻፶፫. ድንግል ማርያም ሐርን ለደብተራ እየፈተለች ወርቅን እየፈተለች ገብርኤል የፍቁር ወልድን መምጣት አበሠራት ይላል። ለመሆኑ ሐር እና ወርቅ ምንድን ነው? ወርቅስ እንዴት ሊፈተል ይችላል?**

መልስ፦ ደብተራ ያላት ቤተ መቅደስን ነው። ይኸውም ቤተ መቅደስ በደብተራ ኦሪት ስለተተካች ነው። አሁን ያሉ እናቶቻችን አክርማውን ቀጭተው፣ ሰበዝ ሰብስበው አገልግል ሙዳይ ሰፍተው ለቤተክርስቲያን እንደሚሰጡ ሁሉ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ለቤተ መቅደስ ሐርንና ወርቅን እያስማማች ትፈትል ነበር ማለት ነው። አሁን በልብሶቻችን ወርቅና ልዩ ልዩ መዓድናትን እያደረግን እንደምንሰፋው ሁሉ ድንግል ማርያምም በሐሩ ላይ ወርቅን እንደጌጥ እያደረገች ትሰፋው ነበር። ወርቅ በቁሙ ወርቅ ነው። ሐር የሚባለው ደግሞ ጥጥ የመሰለ የሐር ትል የሚባል ትል ሸረሪት ድርን እንደምትሠራው እንደ ድር የሚሠራው ነው።

**፻፶፬. በምድር ላይ ሁሉ የደስታ ቃልን የሚናገር ገብርኤል ወደ ገሊላ ሀገር ወደ ማርያም መጣ ሲል ምን ማለት ነው? ገብርኤል የቁጣ ቃል አይናገርም ወይ?**

መልስ፦ በቅዱሳን መላእክት ኀዘን፣ ብስጭት፣ ቁጣ የለባቸውም። መጽሐፍ ቅዱስና አዋልድ መጻሕፍት የመላእክትንና የእግዚአብሔርን ሥራ በሚናገሩ ጊዜ ለሰው ቅርብ በሆነ ቋንቋ ለመግለጽ በሰውኛ ምሳሌ (Metaphorical expression) ይናገራሉ። በዚህ አግባብ ፍርዳቸውን፣ ቅጣታቸውን ለመግለጽ ይቆጣሉ ተባለ እንጂ በመላእክት ዘንድ ቁጣና ብስጭት የለም። በቅዱሳት ነፍሳትም እንዲሁ ነው። ዓለሙ ሁሉ መስማት የሚፈልገውና ቢሰማው የሚያስፈልገው ዜና ነበር። ይህ ዜናም የአምላክ ሰው መሆን ነው። ይህንን ታላቅ ዜና ለሰው ልጆች በመናገሩ ገብርኤል መልአከ ፍሥሐ ይባላል። በምድር ላይ ሁሉ የደስታ ቃልን የሚናገር የተባለበት ምክንያት የክርስቶስ ሰው መሆን ለምድር ሁሉ ደስታ ስለሆነ ይህንን የምሥራች ደግሞ ገብርኤል ስለተናገረው ነው።

**፻፶፭. ማርያምን ሚካኤል መልአክ በክንፉ ተሸከማት ሲል ምን ማለት ነው? ረቂቅ (ሚካኤል) እና ግዙፍ (ማርያም) እንዴት ነው?**

መልስ፦ ረቂቃን መላእክት ግዙፍን የመሸከም አቅም ወይም ኀይል አላቸው። ረቂቁ እግዚአብሔር ግዙፉንም ረቂቁንም ዓለም ይዞት እንደሚኖር የታወቀ ነው። ስለዚህ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ድንግል ማርያምን በክንፉ ይይዛት ነበር ማለት ነው። ጠባቂ መልአኳ እርሱ ቅዱስ ሚካኤል ነበርና።

፻፶፰. ወገቡም ጭኑም በአፌዝ ወርቅ [ያሸበረቀ] ገብርኤል የሚባል አንድ መልአክ አለ ይላል። ኤፌዝ ወርቅ ምንድን ነው? ምስጢሩስ ምንድን ነው?

መልስ፦ አፌዝ ወርቅ የሚገኝበት የወርቅ ቦታ ነው። የአፌዝ ወርቁ ጽሩይ ንጹሕ እንደሆነ ሁሉ የገብርኤል ወገቡና ጭኑ በአፌዝ ወርቅ ያሸበረቀ ነው ማለት ረቂቅ አካሉ ጽሩይ ንጹሕ ነው ማለት ነው እንጂ ለገብርኤል ግዙፍ የወርቅ ልብስ አለው ለማለት አይደለም።

፻፶፱. ኢሳይያስ ሐዳስዩ ጣዕዋ አላት ይላል። ግን ከኢሳይያስ አላገኘሁምና የት አለ? ይቤላ ስንል እንዴት ነው? ለምሳሌ ጽንዕት ምድር ዘኢሳይያስ ጸምር ዘጌዴዎን መሰንቆ ዘዳዊት ጽርሕ ዘሚልክያስ ትባላለች። እነርሱ ስላሏት ነው ወይስ ሊቃውንት በእነርሱ ምሳሌ ሰለመሰሏት?

መልስ፦ እኔም ነቢዩ ኢሳይያስ ድንግል ማርያምን ሐዳስዩ ጣዕዋ ያለበትን ቦታ አላገኘሁትም። አላት የሚለው ግን የሊቃውንት ትርጓሜ ነው። ሊቃውንት በብሉይ ኪዳን የተደረገውን ድርጊት መሠረት አድርገው ከአሁኑ ጋር ምሳሌ አድርገው ይናገራሉ። ይህ መንገድ ራሱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ነውና። ቅዱስ ጳውሎስ በኦሪት ለእስራኤል ውሃ ያፈልቅላቸው የነበረውን ድንጋይ ያ ድንጋይ ክርስቶስ ነው ብሎ እንደተረጎመው (ዘፀ.17፥6፤ 1ኛ ቆሮ.10፥4)። በዚህ አግባብ ነቢያት በዘመናቸው ለሆነ ድርጊት የተናገሩትን ሊቃውንት ልክ እንደ ጳውሎስ ምሥጢሩን አይተው በሐዲስ ኪዳን ለተከናወነ ድርጊት ይጠቅሱታል። ሲጠቅሱም ይቤ፣ ይቤላ፣ ይቤሉ ማለታቸው የሐሳቡ ምንጭ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው።

፻፷. መድኀኒታችን በተድላ መለኮት ተወለደ ይላል። ተድላ መለኮት ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ተድላ ማለት ምቾት፣ ደስታ፣ ሥልጣን፣ መገባት ማለት ነው። ስለዚህ መድኀኒታችን በተድላ መለኮት ተወለደ ማለት በመለኮት ሥልጣን ተወለደ ማለት ነው። ይህንን የመሰለ በቅዳሴ ተጽፏል። "ወረደ እንዘ ኢየዐርቅ በተድላ መለኮት" እንዲል (ቅዳሴ ጎርጎርዮስ)። ለመለኮቱ በሚገባ መንገድ ወይም ለመለኮቱ በሚመች መንገድ ተወለደ ማለት ነው። ለመለኮቱ የሚገባ የሚመች ማለት መለኮት በዘመን ብዛት አይለወጥም። ስለዚህ መለኮት መለወጥ ሳይኖርበት [እንበለ ውላጤ] ሰው ሆነ ማለት ነው። በሥልጣኑ ሳለ ሰውነትን ገንዘብ አድርጎ ተወለደ ማለት ነው።

፻፷፩. ነአምን አበ ፈናዌ ወልደ ተፈናዌ መንፈሰ ቅዱሰ ማሕየዌ ዐቢየ ኖላዌ ሰማያዌ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ አብ ፈናዊ፣ ወልድ ተፈናዊ፣ መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ እንደሆነ እናምናለን ማለት ነው። አብ ፈናዊ፣ መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ መባላቸው ግብረ ባሕርይ ነው። ይህም የወልድ ሰው መሆን የአብም ፈቃድ መሆኑን ለመግለጽ ፈናዊ ተብሏል።

ማሕየዊ የሚለው የሚያድን ወይም የሚያኖር ተብሎ ይተረጎማል። ይህም ከዚህ ላይ ተለይቶ ለመንፈስ ቅዱስ ቢነገርም በማሕየዊነት ሦስቱ አካላት አንድ ስለሆኑ ወልድንም አብንም ይመለከታል። ሦስቱም አካላት ነባቢ፣ አንባቢ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ ይባላሉና። አንባቢ፣ አለባዊ፣ ማሕየዊ ለፍጡራን ስለሆነ አፍኣዊ ግብር (ግብረ ባሕርይ) ነውና። ወልድ ተፈናዊ መባሉ በተለየ አካሉ ሰው የሆነ እርሱ በመሆኑ ነው። ሰው መሆኑን መላክ ብሎታል። ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ላይ አብ በተለየ አካሉ ፈናዊ ይባላል የሚለው ግብረ ባሕርይን ለየአካላቱ አድሎ መናገር ልማደ መጽሐፍ ስለሆነ ነው። አብ አምላክ እንዲል።

፻፳፪. ጌና ማለት ምን ማለት ነው? የታኅሣሥ28 ልደት እውነት ነው? እውነት ከሆነ 7ኛው ጳጕሜን በሆነበት ዘመን ታኅሣሥ 27 ዕለት ልናውለው ልናከብረው ነው? 6ኛይቱ ጳጕሜን መያጢተ በዓል ከሆነች ስለምን የክርስቶስ ልደት ብቻ መለሰች? ልደት በ28 ሲውል ጌና በ27 ይሆናል ማለት ነው? ልደት፣ ገና፣ ጌና ልዩነታቸው ምንድን ነው?

መልስ፡- አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ገና ወይም ጌና ማለት ልደት ማለት እንደሆነ ገልጸዋል። አዎ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ልደት ታኅሣሥ 28 ይከበራል። ይህም የሊቃውንት የሥርዓት ብያኔ ነው። የካቲት 23 ይውል የነበረውን የቃና ዘገሊላ በዓል የውሃን በዓል ከውሃ በዓል ለማያያዝ በማለት ጥር 12 ቀን እንዲከበር አድርገዋል። በዚሁ መሠረት የገና በዓልም ጳጕሜን 5 ዕለተ መድኀኒት፣ ዕለተ ምርያ ትባላለች። እርሷ በዋለችበት ቀን ገና እንዲውል ሥርዓት ስለሠሩ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ታኅሣሥ 28 ይሆናል። ታኅሣሥ 28 ቀን ገና መባሉም ስለዚህ ነው። በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ይውልበታልና። የውሃን በዓል ከውሃ በዓል ብለን ለይተን ቃና ዘገሊላን ከየካቲት 23 ወደ ጥር 12 እንዳመጣነው ሁሉ ዕለተ መድኀኒትን ከዕለተ መድኀኒት ለማያያዝ ከሌሎች ለይተን ገናን ብቻ ጳጕሜን 5 በዋለችበት ዕለት እናከብረዋለን። ሌላው በነበረበት ይከበራል። [በነገራችን ላይ ይህ ሥርዓት ስለሆነ በቅዱስ ሲኖዶስ ሊሻሻልም ይችላል]። ምንም እንኳ በስድስት መቶ ዓመት አንድ ጊዜ ጳጕሜን ሰባት ብትመጣም በቀመር ብቻ ሰባት ትሆናለች ተብላ ትነገራለች ታስባ ትውላለች እንጂ በመደበኛው ስድስት ቀን ብቻ ተደርጋ ስለምታልፍ በዓለ ልደትን ወደ ታኅሣሥ 27 አታወርደውም።

፻፳፫. ሰብአ ሰገልን በቅድስና ሕይወት ነው የምንይዛቸው? ከውዳሴ ማርያም ዘዓርብ ትርጓሜ ኮከብ ብሩህ ዘነጸርዎ ቅዱሳን ይልና ሰብአ ሰገል ካለ በኋላ ቅዱሳንን ጽኑዓን ሲል ነው ይላል።

መልስ፡- ሰብአ ሰገል ቅዱሳን ናቸው የሚል የለም። እንዲያውም ለጌታ እጅ መንሻ አቅርበው ሲመለሱ ድንግል ማርያም ምግብ [የገብስ ዳቦ] ሰጥታ ሸኝታቸው ነበር (ተአምረ ኢየሱስ)። በኋላ ሀገራቸው ከገቡ በኋላ በእሳት የሚያመልኩ ሆነዋል። እንደገና ሐዋርያው ናትናኤል አስተምሮ አጥምቋቸዋል (ማቴ.2፥11 አንድምታ ትርጓሜ)። ኮከብ

ብሩህ ዘነጸርዎ ቅዱሳን ያለውም "ቅዱሳንን" ጹኑዓን፣ ኀያላን ብሎ መተርጎሙ ስለዚህ ነው::

፻፷፬. ሰብአ ሰገል ስለክህነቱ ዕጣን ስለመንግሥቱ ወርቅ ስለሞቱ ከርቤን አመጡለት ይላል:: የጌታ መንግሥት ከወርቅ፣ ሞቱ ከከርቤና ክህነቱ ከዕጣን ምን ያገናኘዋል?

መልስ፦ ለንጉሥ ወርቅ እንደሚገበር ሁሉ ክርስቶስንም ንጉሠ ሰማያት ወምድር ነህ ሲሉ ወርቅ ገብረውለታል:: ካህን ዕጣን አጥኖ ሰውን ከእግዚአብሔር እንደሚያቀርብ ሁሉ ሰውንና እግዚአብሔርን ለማስታረቅ ሊቀ ካህናት ሆኖ በመስቀል ተሰቅሎ ራሱ መሥዋዕት፣ ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ፣ ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ ሆኖ አድኖናል:: በዚህ አግባብ ሊቀ ካህናት ነህ ለማለት ዕጣን አቅርበውለታል:: ከርቤ መራራ ነው:: ስለዚህ ምንም ንጹሐ ባሕርይ ብትሆን መራራ ሞትን ትሞታለህ ለማለት ከርቤን አቅርበውለታል::

፻፷፭. እናቱ በድንጋይ በረት አስተኛችው የበለስ ቅጠልም አለበሰችው ይላል:: በጨርቅ ጠቀለለችውና የበለስ ቅጠል አለበሰችው የሚለው እንዴት ይታረቃል? የድንጋይ በረት የሚለው ምንድን ነው?

መልስ፦ የድንጋይ በረት ማለት ከድንጋይ የተሠራ በረት ማለት ነው:: ድንግል ማርያም ጌታን በወለደች ጊዜ በጨርቅ ጠቅልላ የበለስ ቅጠልም በላዩ ላይ ጣል አድርጋበታለች:: በጨርቅም ጠቅልለዋለች እንዳይበርደው ብላ የበለስ ቅጠልም በላዩ አድርጋለታለች:: ስለዚህ የሚቃረን ነገር የለውም::

፻፷፮. የፈረሰውን ይሠራ ዘንድ፣ ነፍሳትንም ይቤዥ ዘንድ ቸር እረኛ [ክርስቶስ] ከሰማይ ወረደ ሲል ምን ማለት ነው? መቤዠት ምንድን ነው?

መልስ፦ መቤዠት ማለት ዕዳን ከፍሎ ማዳን ማለት ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ዕዳ በመስቀል ከፍሎ አዳምን ስላዳነው ተቤዠው ይባላል:: አዳምን ከመርገም ነጻ አውጥቶ አዳነው ማለት ነው:: የፈረሰውን ይሠራ ዘንድ ያለው በቤት ግሥ ተናግሮት ነው:: የፈረሰ ቤት ሲሠራ አዲስ እንደሚሆን በመርገመ ሥጋ በመርገመ ነፍስ ተይዞ የነበረውን አዳም ክርስቶስ መጥቶ በሐዲስ ተፈጥሮ አድሶታልና ይህንን ለመግለጽ ነው:: ከሰማይ ወረደ መባሉ ሰው ሆነ ተብሎ ይተረጎማል::

፻፷፯. የያዕቆብን ደም ግባት የወደደ [እግዚአብሔር] ነው ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ደም ግባት ያለው ሰው ለተመልካቹ ደስ እንደሚያሰኝ ሁሉ እግዚአብሔርም የያዕቆብን ደም ግባት ወደደ ተብሏል:: ይህም ውጫዊ ደም ግባትን የሚያመለክት አይደለም:: እግዚአብሔር የሚወድ ምግባርን ሃይማኖትን አይቶ ስለሆነ የያዕቆብን ሃይማኖትና ምግባር የወደደ ተብሎ ይተረጎማል:: ምሥጢሩ የያዕቆብ ደም ግባት

የተባለች ከያዕቆብ ወገን የተወለደች ድንግል ማርያም ናት። በምግባሯ በሃይማኖቷ ከሰው ልጆች ሁሉ ብትበልጥ ድንግል ማርያምን እናቱ ትሆን ዘንድ የወደደ ማለት ነው (መዝ.46፥4 ትርጓሜ)።

፸፰. ኢየሱስ ክርስቶስ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ከብርሃን አብ የተገኘ ብርሃን ወልድ ነው ማለት ነው። አብ በባሕርዩ ብርሃን እንደሆነ ወልድም ብርሃን ነውና።

፸፱. ሙሴ የሰበከው የይስሐቅ ቤዛ ይህ ልጅህ ነው ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ክርስቶስ የይስሐቅ ቤዛ ነው የሚለው በምሳሌና በአማናዊ ይተረጎማል። በምሳሌ ይስሐቅ ሊታረድ ሲል በይስሐቅ ፈንታ በግ በዕፀ ሳቤቅ መጥቶ በጉ ታርዷል። ያ በግ የክርስቶስ ምሳሌ ነው፣ ዕፀ ሳቤቅ የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት (ዘፍ.22፥13)። በአማናዊ ሲተረጎም ምንም ይስሐቅ ደግ ሰው የነበረ ቢሆንም እንደሌሎች የብሉይ ኪዳን ደጋግ ሰዎች ሲሞት ሲኦል መግባት አልቀረለትም። ከዚያ ያዳነውና ቤዛ ሆኖ ልጅነትን የሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

፹. ወደ ዓለም የመጣው ብርሃን የጽዮን በኵር ይባላል ሲል ምን ማለት ነው? ጽዮን ሲል ማንን ነው?

መልስ፦ በኵር የሚለው የመጀመሪያ ማለት ነው። ጽዮን ያላት ቤተክርስቲያን፣ ድንግል ማርያም ናት። በምሳሌ ድንግል ማርያምም ቤተክርስቲያንም በጽዮን ይመሰላሉና። ክርስቶስ የድንግል ማርያም በኵር መባሉ ተቀዳሚም ተከታይም የሌለው ልጇ መሆኑን ለመግለጽ ነው። የቤተክርስቲያን በኵር መባሉ ለልጅነት፣ ለትንሣኤ ሙታንና ለመሳሰሉት በኵር በመሆኑ ነው።

፹፩. ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም መጥቷልና ኑ በብርሃኑ እንመላለስ ይላል። በብርሃኑ እንመላለስ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ የክርስቶስ ብርሃን የተባለች ያስተማራት ወንጌል ናት። በብርሃኑ እንመላለስ ማለት በወንጌል እንኑር ማለት ነው። ይኸውም ምግባር ትሩፋትን እንሥራ ማለት ነው።

፹፪. አዳም ያገለደመው በለስና እመቤታችን ጌታን ያለበሰችው በለስ አንድ ዓይነት ነው?

መልስ፦ አላውቀውም።

፹፫. ክርስቶስን ለእኛ የተሰጠ የተሠወረ መዝገብ ነው ሲለው እንዴት ነው?

መልስ፦ ክርስቶስ የተሠወረ መዝገብ ይባላል። ይህም የተሠወረን መዝገብ ሁሉ እንደማያገኘው ክርስቶስንም ያመነበት እንጂ ያላመነበት አያገኘውምና ነው። መዝገብ መባሉ በመዝገብ ብዙ ወርቅ እንደሚገኝ ከክርስቶስም ለምእመናን የሚሰጥ ብዙ ጸጋ አለና።

**፻፸፬. ሥጋዋን አንጽቶ በእርሷ አደረ የሚለው ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ሥጋዋን አንጽቶ የሚለው አነጋገር እስከ ጽንሰተ ክርስቶስ በመርገም ቆይታ በኋላ አንጽቶ ተጸነሰ ማለት አይደለም። ከሰው ልጆች ሁሉ ደግ እንደምትሆን በመለኮታዊ ዕውቀቱ አውቆ ከእናቷ ማሕፀን ጀምሮ ንጽሕት አድርጎ ጠብቋታል። ይህንን መጠበቁን ለመግለጽ ቅዱስ ያሬድ አንጽቶ ብሎ ገልጾታል። ከእናቷ ማሕፀን ጀምሮ ጠብቆ ማለት ነው።

**፻፸፭. ዘመነ ሐዲስ ከጽንሰተ ክርስቶስ ጀምሮ ነው። ስለምን እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕተ ይባላል? ሕፃናተ ገሊላ ቀድመው ሰማዕት ሆነው የለምን? ከካሣ ወዲህ (ከክርስቶስ ሞት ወዲህ) ነው ከተባለ እነለንጊኖስ በትንሣኤ ውስጥ እንደሞቱ ይነገራልና እንዴት ነው?**

መልስ፦ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት (የሰማዕታት መጀመሪያ) የተባለው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመጻፍ ነው። ይህ ደግሞ "ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ። ክብሩንም ገለጠ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ" ከሚለው ጋር ይመሳሰላል (ዮሐ.2፥11)። እንጂ በተአምረ ኢየሱስም፣ በተአምረ ማርያምም እነ ጊጋር መስፍንን የመሰሉ ሰማዕታት ቀድመው እንደሞቱ ተጽፏል። ሆኖም ከመጀመሪያዎቹ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጻፍ እስጢፋኖስ ስለሚቀድም ቀዳሜ ሰማዕት ተብሏል።

**፻፸፮. በስምንተኛ ቀን ይገዝሩት ዘንድ ሕፃኑን ወሰዱት ስሙንም አማኑኤል አሉት ይላል። ሉቃ.2፥21 ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ ይላል። ሁለቱ አይቃረንም?**

መልስ፦ አይቃረንም። በስምንተኛው ቀን ሲገዝር የተሰየመው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው "ኢየሱስ" ተብሎ ነው። አማኑኤል እየተባለ የሚጠራውም ግን ያው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለመግለጽ ቅዱስ ያሬድ "አማኑኤል" ተባለ ብሎታል።

**፻፸፯. ከያዕቆብ ወገን የወጣ የቅዱሳን ፀሐይ ክርስቶስ የሃይማኖት ጥሩር ነው ሲል ምን ማለት ነው? የያዕቆብ ወገን ሲል ምን ማለት ነው? ጥሩር ምንድን ነው?**

መልስ፦ ጥሩር የሚባለው በቀድሞው ዘመን ራስን ከጦር፣ ከቀስት ለማዳን የሚደረግ የራስ ቁር ነው። ይህም ለዐይን ማያ ብቻ ጥቂት ቀዳዳ ኖሮት እንደቆብ ያለ ከአንገት በላይ ያለውን አካል ሁሉ የሚሸፍን የብረት ልብስ (ቆብ) ነው። ክርስቶስም ከጠላት ሰይጣን የዳንንበትና የምንድንበት በመሆኑ የሃይማኖት ጥሩር ተብሏል። ክርስቶስ

የያዕቆብ ወገን፣ የዳዊት ወገን፣ የአብርሃም ወገን እየተባለ ይጠራል። እንዲህ የተባለው እነርሱ አያት ቅድመ አያቶቹ ስለሆኑና በዘር ሐረግ ከእነርሱ ስለሚወለድ ነው።

፻፴፰. ሞትን ያልቀመሰ ዮሐንስ ድንግል ወገቡን በጌታው መታጠቂያ ታጠቀ ይላል። በጌታው መታጠቂያ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ አሁን መነኮሳት እንደሚታጠቁበት ያለ ጌታ ወገቡን የሚታጠቅበት መታጠቂያ ዝናር ነበረው። ያንን መታጠቂያ አንድ ቀን ዮሐንስም ታጥቆት በዚህ ምክንያት ፍትወት እንስሳዊት ጠፍታለታለችና ይህን ለመግለጽ ነው (መጽሐፈ ቅዳሴ ትርጓሜ)።

፻፴፱. ከልጅነቱ ጀምሮ ያለበደል ያደገ፣ ከእሳት አጠገብ የተቀመጠ ዮሐንስ ነው ሲል ምን ማለት ነው? ሰው ሆኖ የማይበደል አለ ወይ? ከእሳት አጠገብ ሲልስ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደበደለ የተገለጸበት ቦታ የለም። ያለበደል መባሉ ስለዚህ ነው። ደግነቱ ግን በወንጌልም በሌሎችም መጻሕፍት ተገልጿል። ሰው ሆኖ ያለበደል ንጽሕናን ጠብቆ መኖር ይቻላል። እግዚአብሔር በበደሉት ላይ ገሃነምን የሚፈርድበት ምክንያት ላልበደሉት ደግሞ መንግሥተ ሰማያትን የሚሸልምበት ምክንያት ለሰው ልጅ አለመበደል የሚችልበትን ክሂል ስለሰጠው ነው። ከእሳት አጠገብ ተቀመጠ ማለቱ እሳት ያለው ክርስቶስ ነው። እሳተ መለኮት ገንዘቡ ነውና። ከክርስቶስ አጠገብ ተቀመጠ ማለት ነው።

፻፵. አብ ወልድን ቅድመ ዓለም ሲወልደው አንድ ጊዜ ነው?

መልስ፦ አዎ። በሃይማኖተ አበው "ወኢየኀልቅ ልደቱ እምኔሁ" ይላል (ሃይ.አበ.13፥24)። ይህም ማለት ሁልጊዜ ወልድ ሲባል ይኖራል ማለት ነው እንጂ ሁልጊዜ ሲወለድ ይኖራል ማለት አይደለም። ሳዊሮስ ዘእስሙናይንም ከፀሐይ ክበብ ብርሃን ያለማቋረጥ እንደሚወጣ ወልድም ከአብ ያለማቋረጥ እንደሚወለድ ገልጿል። ይትወለድ የሚለው ካልኣይ አንቀጽ በቀዳማይ አንቀጽ ተወልደ ተብሎ መተርጎም ስለሚችል ያለማቋረጥ ተወለደ ተብሎ ይተረጎማል። ካልኣይ በቀዳማይ ቀዳማይ በካልኣይ ይተረጎማልና። ለዚህም ማስረጃው አመ ይወፅኡ እስራኤል እምግብጽ የሚለው ነው። አመ ወፅኡ ማለት ነውና። ያለማቋረጥ (እንበለ ተመትሮ) ተወለደ የሚለውም እናት ልጇን ስትወልድ በህልውና ከእርሷ ይለያል ተመትሮ አለበት። ወልድ ከአብ ሲወለድ ግን በህልውና ከአብ ሳይለይ ነውና ይህንን ለመግለጽ ነው።

፻፵፩. አቡቀለምሲስ ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፦ አቡቀለምሲስ የተባለ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው። ትርጉሙም ረኣዪ ኅቡዓት ማለት ነው። ይህም ምሥጢርን ያየ፣ የሚያይ ማለት ነው።

**፻፹፪. ዮሐንስን ደስ የሚያሰኝ ምሥጢርን ያየህ በምድር ያለህ መልአክ ነህ ሲለው እንዴት ነው? መልአክ እንዴት ተባለ?**

መልስ፦ ተፈጥሮው ምድራዊ ሆኖ በተግባር መላእክትን የመሰለ ሰው መልአክ ዘበምድር ይባላል፡፡ ለምሳሌ መላእክት ሥጋዊ ምግብን አይበሉም፡፡ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ከሥጋው ከደሙ በቀር ምግብን አይበላም ነበረ፡፡ በዚህ ምክንያት መልአክ ዘበምድር ይባላል፡፡ ዮሐንስም ፍትወት እንስሳዊት የጠፋለት በመሆኑና ንጽሕናው እንደመላእክት ስለነበር መልአክ ዘበምድር ተብሏል፡፡

**፻፹፫. ማርያምም እስኪ ጠይቁ ብነግራችሁ ከአፌ እሳት ወጥቶ ዓለምን ሁሉ ያጠፋል አለቻቸው ይላል፡፡ እንዴት? ነቢያት ማርያምን እንደጠየቋት ይናገራል፡፡ ሳይኖሩ እንዴት?**

መልስ፦ ድንግል ማርያም በክብር ከፍጡራን በላይ ናት፡፡ ለእርሷ የተገለጠውን ምስጢር ለሌላው ብትናገር የሌላው ፍጥረት ያንን ምስጢር የመስማት አቅም ዝቅተኛ ስለሆነ ብናገር ከአፌ እሳት ወጥቶ ዓለምን ያጠፋል ብላለች፡፡ ለምሳሌ በትንሽ አምፖል ብዙ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኀይል ብንለቅበት ይቃጠላል፡፡ አምፖሉ የሚቃጠለው ከአቅሙ በላይ የሆነ ኀይል ስለተለቀቀበት ነው፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሰማችውን ምሥጢር ሌላው ፍጥረት መስማት አይችልም፡፡ እንዲያውም በአንድ ወቅት ሐዋርያት ነገሪን ብለዋት ታሪኩን ልትጀምርላቸው "ቀኑ ካፊያ ነበረ፣ ወትሮ የማውቀው መልአክ ቀርቶ ሌላ መልአክ መጣ" ብላ ወደ ምስጢሩ ልትገባ ስትል የመልአክ ድምፅ ተሰማ፡፡ ያን ጊዜ ሐዋርያት እንደ ቅጠል ረገፉ ይላልና (የማክሰኞ ውዳሴ ማርያም አይ ልሳን ትርጓሜ)፡፡ ነቢያት ጠየቋት ማለቱ ሰብአ አርድእትን ነቢያት ስለሚላቸው ሰብአ አርድእትም ጠየቋት ማለት ነው፡፡

**፻፹፬. የርስታችን ፈለማ ፍጹም ውበታችንና ሽልማታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሲል ፈለማ ምንድን ነው?**

መልስ፦ ፈለማ ማለት ዋናው ከመሰጠቱ በፊት የሚሰጥ ቅምሻ ማለት ነው፡፡ ለክርስቶስ ሲነገር ግን ዋናውም ቅምሻውም ራሱ ነው፡፡ ታዲያ ቅምሻ መባሉ ስለምን ነው ከተባለ በዚህ ምድር ሰጥቶን የሚኖረው ጸጋ በኋላ በመንግሥተ ሰማያት ከምናገኘው ጸጋ ስለሚያንስ ነው፡፡ ፈለማ ከዚህ ከሚሰጠን ጸጋ አንጻር የሚተረጎም ነው ማለት ነው፡፡ እንጂ ክርስቶስ በዚህም በዚያም አንድ ነው፡፡

**፻፹፭. ከዕሴይ ሥር የክብር ፍሬ ወጣ ሲል ምን ማለት ነው? ዕሴይ ምንድን ነው?**

መልስ፦ ዕሴይ የዳዊት አባት ነው፡፡ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ ዕሴይም ከቅድመ አያቶቹ አንዱ ነው፡፡ የዕሴይ ሥር የተባለች ድንግል ማርያም ሲሆን ከእርሷ የተገኘው የክብር ፍሬ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ሥር ካለ ዘንድ ፍሬ አለ እንጂ ወርቁ ክብር

የሚለው ነው። ክርስቶስ በባሕርዩ ክቡር ስለሆነ ከዚህ ክብር ተብሏል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው እንደሚለው ነው (1ኛ ዮሐ.4፥16)።

**፻፴፮. ክርስቶስ በነጭ ወፍ የተመሰለበት ምክንያት ምንድን ነው?**

*መልስ፦ ይህ ነጭ ወፍ በልዩ ስሙ ከራድዮን ይባላል። በታመመ ሰው ፊት ያኖሩት እንደሆነ አፉን ከአፉ ገጥሞ የታማሚውን እስትንፋስ ይወስዳል። ከዚያ ነጭ የነበረው ወፍ ከሕመሙ የተነሣ ይጠቁራል። ብርድ ብርድ ሲለው ወደ አየር ከፍ ብሎ በርሮ ራሱን የፀሐይ ብርሃን ያስመታል። ከዚያ ሦስት ቀን በባሕር ቆይቶ በሦስተኛው ቀን እንደበፊቱ ነጭ ሆኖ ይመለሳል። ጌታም የታማሚውን አዳም ባሕርይ ባሕርይ አድርጎ ስለአዳም በመስቀል ተሰቅሎ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ ባለመታመም ግብር ጸንቶ ኖሯልና ክርስቶስ በነጭ ወፍ ተመስሏል (የአርብ ውዳሴ ማርያም ቡርክት አንቲ ተዐብዩ እምሰማይ ትርጓሜ)።*

**፻፴፯. ዙፋኑ በኢዮር ላይ የሆነ መመላለሻው ደመና የሆነ፣ አዳራሹ የእሳት፣ ጣሪያው የውሃ የሆነ እግዚአብሔር ነው ሲል ምን ማለት ነው?**

*መልስ፦ ኢዮር ከመላእክት ከተሞች የላይኛው ከተማ ነው። ዙፋኑ በኢዮር ላይ የሆነ ማለት ዙፋኑ ልዑል [ታላቅ] የሆነ ማለት ነው። አዳራሹ የእሳት የተባለው ባሕርዩ ራትዕ የሆነ ማለት ነው። ጣሪያው የውሃ ማለት ባሕርዩ መንጽሒ የሆነ ማለት ነው። ደመና መመላለሻው የሆነ ማለት በባሕርዩ ልዑል የሆነ ማለት ነው። "ዘበእንተ ዕበይከ ትትሜሰል በደመና" እንዲል። ሁለተኛው ትርጉሙ ደግሞ እንዳለ ይሆናል። እግዚአብሔር በዘፈቀደ የሚገለጥበት ዙፋን ከኢዮር በላይ ባለ በመንበረ ስብሐት ይገኛል። መመላለሻው የደመና፣ አዳራሹ የእሳት፣ ጣሪያው የውሃ ነው። ይህም ለብዙ ቅዱሳን በተገለጠላቸው መናገራችን እንጂ በዚህ ብቻ የሚወሰን አይደለም።*

**፻፴፰. ቃል በቃሉ ተናገራት በመልአክ አምሳያ ታያት ሲል የተገለጸላት መልአኩ አይደለም ማለት ነው?**

*መልስ፦ የተገለጸላት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ነው። ቃለ እግዚአብሔር ደግሞ በገብርኤል አድሮ ተናግሯታል። አካላዊ ቃል በገብርኤል አድሮ ትወልዲ በሚል በሚሰማ ድምፅ (ዝርው ቃል/ቦርፎሪኮን) ተናገራት ማለት ነው። በገብርኤል አድሮ የተናገረ ቃለ እግዚአብሔር ስለሆነ ባለቤቱን ቃል ብሎታል። በቃሉ ብሎ ደግሞ በማድረጊያ የተናገረው ትወልዲ በሚለው ዝርው ቃል ተናገራት ለማለት ነው።*

**፻፴፱. ዘጠና ዘጠኙን ነገድ ትቶ ከሰማያት ወረደ ሲል ምን ማለት ነው? መቶ ነገድ የሚባለው እንዴት ነው? 99 ነገድ ለምን ተባሉ?**

መልስ፦ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የሚኖር አምላክ ስለሆነ አንዱን ለመፈለግ ሌላውን አይተውም። ስለዚህ ትቶ የሚለው አገላለጽ ባሕርያቸውን ሳይዋሐድ ተብሎ ይተረጎማል። የ99ኙን ነገደ መላእክት ባሕርይ ሳይዋሐድ ለይቶ የሰውን ባሕርይ ተዋሐደ ማለት ነው። "ኢነሥአ ለዘነሥአ እመላእክት ዘእንበለ ዳእሙ እምዘርአ አብርሃም" እንዲል (ዕብ.2፥16)። መላእክት ሲፈጠሩ መቶ ነገድ ነበሩ። አንዱ ነገድ ግን ከሳጥናኤል ጋር ወድቋል። በዲያብሎስ ምትክ ሰው ገብቷል። ሰውም ወደቀ። ነገር ግን ንስሓ በመግባቱ ባሕርዩን ተዋሕዶ አምላክ አድኖታል።

## ፻፺. ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው በጥምቀቱም ውሃ ተቀደሰ ይላል። ውሃ ርኩስ ነበረ ወይ? ከምን አንጻር ነው ተቀደሰ ያለው?

መልስ፦ ውሃ ርኩስ አልነበረም። ነገር ግን በብዙዎች ዘንድ እንደ ርኩስ ይታይ ነበር። ለዚህ መነሻ የሆነውም በኖኅ ዘመን የዓለም በንፍር ውሃ መጥፋት ነው (ዘፍ.7፥6)። ይህ ብቻ ሳይሆን ውሃ በነፍሳዊው ሕይወት ምንም ፋይዳ አልነበረውም። ክርስቶስ ሰው ሆኖ በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ ግን ውሃ ተቀድሶበት ልጅነትን ለማግኘት ምክንያት ሆኗልና ተቀደሰ ተብሏል (ዮሐ.3፥5)። በጥምቀት ካህኑ ከቀደሰበት በኋላ ወደ ማየ ገቦ ተለውጦ ልጅነትን የምናገኝበት ሆኗልና።

## ፻፺፩. ከዓለም በፊት ብርሃንን የፈጠረ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ዓለም የሚለው ቃል በብዙ መንገድ ይተረጎማል። ከብዙዎች መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት። አንደኛ ፍጥረታት ሁሉ ዓለም ይባላሉ (መዝ.90፥11)። ሁለተኛ ኃጢአት ዓለም ይባላል። "ኢታፍቅርዎ ለዓለም ወኢ ዘሀሎ ውስተ ዓለም ወዘሰ አፍቀሮ ለዓለም ኢሀሎ ፍቅረ እግዚአብሔር ላዕሌሁ" እንዲል (1ኛ ዮሐ.2፥15)። ሦስተኛ ዓለም የሚባለው ሰው ነው። "እስመ ከመዝ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም እስከ ወልዶ ዋሕደ መጠወ ወወሀበ ቤዛ ለኵሉ ከመ ኵሉ ዘየአምን ቦቱ ኢይትኀጐል አላ ይረክብ ሕይወተ ዘለዓለም" እንዲል (ዮሐ.3፥16)። ከዓለም በፊት ብርሃንን የፈጠረ የሚለው በሦስተኛው የሚተረጎም ነው። ይህም ማለት ከሰው በፊት ብርሃንን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው።

## ፻፺፪. ሙሴና ዳዊት ጠል ያሉት ቃልን ማርያም ወለደችው ሲል ምን ማለት ነው? ጠል የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው?

መልስ፦ ሙሴና ዳዊት ቃለ እግዚአብሔርን ጠል ያሉት ከፀምር አንጻር ነው። ጠል እንደ ጤዛ በደመና ጊዜ ብናኝ መስሎ ወደ ምድር የሚወርድ ነው። በዚህ ጊዜ ፀምር ከመሬት ካለ ጠሉ ከፀምሩ ላይ ያርፋል። ጠል የደረቀውን እንደሚያለመልም ክርስቶስ በኃጢአት ደርቆ የነበረውን ዓለም አድኖታልና ነው። ጠሉ በፀምር እንዳረፈ ቃለ እግዚአብሔርም

በድንግል ማርያም ማሕፀን ተፀንሶ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ኖሯልና ፀምር የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው።

፻፺፫. ከእኛ ተሠውሮ ሲኖር ዛሬ ግን የተገለጠ ሆነ ውሃውንም ወይን አደረገው ይላል። ወይን ሲል ምን ማለት ነው? ተሠውሮ ሲኖር ማለትስ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ወይን የተባለው በቁሙ ወይን ነው። ጌታ በቃና ዘገሊላ ውሃውን ወደ ወይን ለውጦታልና (ዮሐ.2፥1-11)። በምስጢር ደግሞ ወይን የተባለ የክርስቶስ ደም ነው። "ምንትኑ ሕይወቱ ለዘኢይሰቲ ወይነ እስመ ውእቱ ለትፍሥሕተ እጓለእመሕያው ተፈጥረ" እንዲል (ሲራ.34፥27)። ተሠውሮ ሲኖር ያለው እግዚአብሔር ሳይታይ ይኖር ነበርና ነው። ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ ግን በሥጋው ታይቷልና ይእዜሰ ክሡተ ኮነ አለ።

፻፺፬. ቴዎድሮስ ማለት መሥዋዕት ማለት ነው ይላል። ይህ ዓይነት አተረጓጎም እንዴት ነው? ስሙ ራሱ መሥዋዕት ማለት ነው? ኃያል ቴዎድሮስ የቃል ሰማዕት ነው ሲል የቃል ሰማዕት ማለት ምን ማለት ኘው?

መልስ፦ በትርጓሜ ብዙ ዓይነት ስልቶች አሉ። አንደኛው ቃላዊ ትርጓሜ ነው። በቃላዊ ትርጓሜ ቴዎድሮስ የግሪክ ቃል ሲሆን በአማርኛ የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው። ሁለተኛው የትርጓሜ መንገድ ግብራዊ ትርጓሜ ነው። ይህም ማለት የሰዎችን ግብር መሠረት አድርገን የምንተረጉመው ትርጓሜ ነው። ለምሳሌ ይሁዳ ማለት ከሓዲ ማለት ነው ብንል ግብርን መሠረት ያደረገ ትርጓሜ ይባላል። ቴዎድሮስ ማለት መሥዋዕት ማለት ነው የሚለው ትርጉምም ግብራዊ ትርጓሜ ነው። እውነትን በመመስከር ለእግዚአብሔር ራሱን የከበረ መሥዋዕት አድርጓልና ነው።

፻፺፭. የከበረ ደሙንና እኛን የሚያነጻን ውሃን [ማየ ገቦን] ሰጠን ሲል ምን ማለት ነው? ጠበል፣ ውሃ እና ማየ ገቦን እንዴት እንገልጻቸዋለን?

መልስ፦ ማየ ገቦ የሚለው ቃል በአማርኛ የጎን ውሃ ማለት ነው። ይህም ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ለንጊኖስ ጎኑን በወጋው ጊዜ ከጎኑ ውሃና ደም ወጥቶ ነበር። ውሃው ማየ ገቦ ይባላል። "አሐዱ እምሐራ ረገዞ ገቦሁ ዘየማን በኲናት። ወሶቤሃ ወፅአ እምኔሁ ደም ወማይ" እንዲል (ዮሐ.19፥34)። አሁን ካህናት ጸሎት አድርገውበት ሕፃናትን የሚያጠምቁበት ውሃ በእግዚአብሔር ቸርነት በዕለተ ዓርብ ከጌታ ጎን የፈሰሰውን ውሃ ሆኖ ልጅነትን ያሰጣል። ጠበል የሚባለው የተቀደሰ ውሃ ነው። ይህም የሰው ልጆች ፈውስ የሚያገኙበት ውሃ ነው። በውሃነት ሁሉም ውሃ ቢሆኑም ነገር ግን ለሰው ልጆች ባላቸው ጥቅም ይለያያሉ። ማየ ገቦ ልጅነትን፣ ጠበል ፈውስን የምናገኝበት ሲሆን ሌላው ውሃ ደግሞ እየጠጣነው፣ ልብስ እያጠብንበት...ወዘተ የምንጠቀምበት ነው።

**፻፺፮. ማርያም እንተ ዕፍረትን ስሚንም በዓለም ሁሉ ያስቡ ዘንድ አደረገ ሲል ምን ማለት ነው? የሌሎች ስምስ እንዴት ነው የሚታሰበው?**

*መልስ፦ ማርያም እንተ እፍረት የተነሣሕያን አብነት ስለሆነች የእርሷ ግብር ለሌላው ትውልድም ቢነገር አስተማሪ መሆኑን ጌታ ስላወቀ ይነገር ብሏል (ማቴ.26፥13)። የሌሎች ቅዱሳን ታሪክም ለእኛ ለሰው ልጆች አርአያ ይሆን ዘንድ ተጽፎ ይነገራል። ለዚህም አብነታችን ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በብሉይ ኪዳን የብዙ አባቶች ማለትም የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ...ወዘተ ታሪክ ተጽፏል። በሐዲስ ኪዳንም የሐዋርያት ሥራን ብንመለከት የእስጢፋኖስ፣ የጳውሎስና የሌሎችም ታሪክ ተጽፏል። ከዚያም በኋላ የተነሡ አባቶች ታሪክ በድርሳናት፣ በገድላት ተጽፎ ይቀመጣል። ስለዚህ የማርያም እንተ እፍረትን ብቻ ሳይሆን ቅዱሳንን ሁሉ እናከብራለን መልካም ሥራቸውንም እየተናገርን እንመሰክራለን።*

**፻፺፯. የክርስቶስ መለኮት ውበት መገለጥ ሆነ ሲል ምን ማለት ነው?**

*መልስ፦ የመለኮት ውበት ያለው ግብረ መለኮትን ነው። የክርስቶስ የመለኮት ውበት ታወቀ ማለት አምላካዊ ሥራው ታወቀ ማለት ነው። ይኸውም ዕው*ራንን በማብራት፣ የተራቡትን በማጥገብ፣ ሕሙማንን በመፈወስ፣ ተአምራትን በመሥራት አሳይቷልና ነው።*

**፻፺፰. እንደሰው ሁሉ ሞት በኀበኛት ጊዜ የአምላክ እናት እንዴት አለቀሰች ይላል። ቅዱስ ጳውሎስ ልሄድ ከክርስቶስ ጋር መኖር ይሻለኛል እያለ ይደሰት ነበር። እንዴት ነው ሞትን የፈራችው? በወንጌል ለቅዱሳን ሞት ያስፈራል?**

*መልስ፦ ሞት ያስፈራልም አያስፈራምም። መፍራት ኃጢአት አይደለም። ድንግል ማርያምን ከሞት በፊትም ሄሮድስ ልጇን ይገድልብኛል ብላ በመፍራት እሾሁ እየወጋት፣ ውሃ እየጠማትና በመሳሰሉት ከሄሮድስ ሠራዊት በመሸሽ አሳልፋለች። ሞትም እንግዳ በመሆኑ ፈርታለች። ለሰው ልጆች ሞትን መፍራት ተፈጥሯዊ ነው። ክርስቶስም ሰው እንደመሆኑ ፈራ ተብሏል። "ወፈርሀ ወአውተረ ጸልዮ" እንዲል (ሉቃ.22፥44)። የእርሱ መፍራት ፍርሀተ ነፍስን ከእኛ ለማራቅና ለቤዛነት ቢሆንም በሰውነቱ መፍራቱ በደል አያሰኝምና ነው። ቅዱስ ጳውሎስም ወደ ክርስቶስ ለመሄድ እቸኩላለሁ ማለቱ የሁሉም ክርስቲያን ፈቃድ ቢሆንም ሞትን አልፈራም የሚል አረዳድን ግን አያመጣም። ሞትን ይፈራሉ። የሚፈሩት ግን ሞትን መፍራት ተፈጥሯዊ ስለሆነ እንጂ በመጠራጠር አይደለም።*